ማስታወሻ

ልጄ ሆይ!

ከውለሞች ጋር በቀልብህ ተገኝ፤

ከመሪዎች ዘንድ ስትቀርብ ዕውቀት ይዘህ ቅረብ፤

ከወዳጆችህ ጋር አደብ ይኑርህ፤

ለቤተሰቦችህ ርህራሄ አይለይህ፤

አላዋቂዎች ዘንድ ታገስ፤

ከጌታህ ጋር ብዙ መቆየት ካሰብክ ዚክር ማድረግ አይለይህ፤

ራስህን በራስህ የምትመክር ብልህ ሁን።

መልካም ሠርቼ አመድ አፋሽ ሆንኩ አትበል፤ ልፋትህ ምድር ላይ ትኩረት ቢያጣም በሰማይ ቤት ተመዝግቧልና አትዘን።

ልጄ ሆይ! ማንኛውም ነገር ለሁለት ስትከፍለው ያንሳል፤ ደስታ ሲቀር።

ደስታን ግን ከሌሎች ጋር ስትካፈለው ይበዛል።

ከአላህ ጋር ሰድግት

አንድ በዕድሜው ወጣት የሆነ ቅልጥ ያለ ‹ዛኪር› ጓደኛ አለኝ። ውይ ታድዬ! .. የሌለኝን ነገር እሱ ስላለውና ስለተሠጠው መፅናኛዬ ነው። ለራስ ቢያጡ ከጎረቤት ይቀላውጡ ነው ነገሩ። ጓደኛዬ የህከምና ዶከተር ነው። ስፔሻሊስትም ነው። መማር ከአላህ ያላራቀው፣ መመራመር በአምላኩ ያልለወጠው ጉደኛ ጓደኛ። ድሮም ሶፈል አወል አሁንም ሶፈል አወል። ድሮም ቁርአን መቅራት አሁንም ቁርአን መቅራት። ድሮም መስጊድ መመላለስ አሁንም መስጊድ መመላለስ። ድሮም የአላህ ሰዎችን መውደድ ዘንድሮም የአላህን ሰዎች መውደድ። አምናም የሚተናነስ ልጅ ነበር ዘንድሮም ይተናነሳል። ካቻምናም ኩፍይት ይለብስ ነበር አሁንም ኩፍይት ይለብሳል። ጁሙዓን ከሁሉ ቀደም ብሎ ምንጣፉን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ ጀለቢያውን ለብሶ ማልዶ ወደ መስጊድ ያዘግማል። በረመዷን ለሚባዳ ብሎ ዕረፍት ይወጣል። በመረዋ ድምፁ ተራዊሕ ያሰግዳል። “ምኑም የተማረ አይመስልም ይሉታል” አንዳንዶች። መማር ማለት ትርጉሙ ከአላህ መራቅ ይመስል። መማር ማለት ዲንን መጣል ይመስል!።

ባለፈው ሱብሒ ላይ የሆነ ሰው አየውና “እዚህ ምን እግር ጣለህ?” አይለውም መሠላችሁ!? የቀረበለት ጥያቄ ገረመውና ነገረኝ። አንዳንዶች እኮ አላህ ማለት የድሃ አምላክ ብቻ ይመስላቸዋል። አንዳንዶች እኮ ሃይማኖትን ያልተማረ ሰው ርስት ያደርጉታል። እናም የተማረ ሰው መስጊድ ከመጣ ይደንቃቸዋል። መስጊድ ሲገባ ነቢይ የገባ ያህል ይጠቋቆማሉ። ደስም ይላቸዋል፤ ለዲን ሰዎች ካላቸው አከብሮት በላይ ለሱ የሚኖራቸው አከብሮት ይጨምራል።

አነርሱ “የተማረ ነው!” ይሉታል። በየደዕዋው እንደ ሞዴልና ማጣቀሻ ያቀርቡታል። አርሱን አይተው መስጊድ የመጡ አሉ። በሱ ቀንተው ወደ አስልምና የተቀኑም አሉ። በባህሪው ተገርመው እንደሱ ለመሆን የተመኙም አሉ። እሱ ግን በራሱ ላይ ምንም ለውጥ አይታየውም። በተለየ ከፍታ ውስጥም ራሱን አያገኘውም። ድሮም ሙስሊም አሁንም ሙስሊም። ድሮም የአላህ ባርያ አሁንም የአላህ ባርያ። ድሮም ከአላህ ጋር አሁንም ከአላህ ጋር። የትከከለኛ ሙስሊም ባህሪ የወረሰ ጥሩ ሙስሊም ነዋ!

እኔ የምለው... ዶ/ር አምላክ የለውም ያለው ማነው? ዶ/ር አይሰግድም፣ አይፆምም፣ አላህን አይፈራም... ያለ ማነው? ዶ/ር ሃይማኖትም ሆነ አምላክ የለውም ያለ ማነው? ዶ/ር ከአምላኩ ፈላጊ ድሃ አይደለም ያለ ማነው? ዶ/ር የሰው ልጅ አይደለም እንዴ?

ለነገሩ በነርሱም ላይፈረድ ይችላል። ስንቶች ናቸው በማግኘታቸው ብቻ ከመስጊድ የራቁ!። ስንቶች ናቸው ተማርን፣ አወቅን፣ ትልቅ ደረጃ ደረስን ብለው ዓሊም የናቁ። ስንቶች ናቸው ቦታችን ከተርታው መደብ አይደለምና በተርታው ሰው መሃል መገኘት የለብንም ብለው በቤታቸው የተደበቁ!!።

ወዳጆቼ እናስታውስ!... መስጊዶች የድሃም የሀብታምም ናቸው። የአላህ ቤቶች የልጅም የአዋቂም ናቸው። የተማረውም ያልተማረውም ሰው ሀሉ ከአላህ ፊላጊ ደሃ ነው። በዕውቀት፣ በገንዘብና በኑሮ ደረጃ ይበላለጥ እንጂ የሰው ልጅ ሁሉ ከፊጠረው ጌታ ከአላህ (ሱ.ወ.) ፈላጊ ነው። ከርታታ፣ ሚስኪን፣ ያልሞላለት ደሃ ነው። ሐኪም ሲታመም አላህን ይለምናል፤ ሀብታም ሲጨንቀው ለድሃ ይመፀውታል፤ ምሁር ግራ ሲገባው በአላህ መኖር ያምናል፣ ባለሥልጣን ከወንበሩ ሲወርድ ለአምላኩ ያጎበድዳል።

እናም ልብ እንበል ... ምሁር ተብሎ የሚታወቅ ሰው መስጊድ ቢመጣ፣ ባለሥልጣን ሶፈል አወል ላይ ቢገኝ፣ ሀብታም ከድሆች እኩል አላህ ፊት ቢቆም... የሆነ የተለየ ነገር እንደተፈጠረ አታስቡ። እነርሱም ሰው እናንተም ሰው። እርሱም ድሃ እናንተም ድሃ መሆናችሁን አትዘንጉ።

ትምህርት ከአላህ ያራቀው ሰው በርግጥም አልተማረም። ገንዘብ ከመስጊድ ያስቀረው ሰው አልከበረም። ሥልጣን ከሰው እንዳይቀላቀል ያገደው አልኖረም።

ታዋቂ ሰዎች ደረጃቸውን ይጠብቃሉ፤ ስልክ አያነሱም፣ ሃብታሞች ጊዜ የላቸውም መልዕክት አይመልሱም። ባለሥልጣናት ተራ ሰዎች መካከል መታየትን አይፈልጉም። የአላህ ባሮች ግን እንዲህ አይደሉም። ትንሽ ትልቁን ያወራሉ፤ ለሚያውቁትም ሆነ ለማያውቁት ሁሉ ይተናነሳሉ። ከድሃ የሚያርቅ ሃብት፣ ከተርታው ሰው የሚያገል ሥልጣን፣ በነፃነት የማያንቀሳቅስ ታዋቂነት ጥንቅር ብሎ ይቅር።

ከአላህ ሥም ፣ አል-ዐፉው፣ ጋር

ከአላህ (ሱ.ወ.) ሥሞች መካከል አንዱ ‹አል-ዐፉው› የሚለው ነው። ‹አል-ዐፉው› "ይቅር ባይ የሆነ አምላክ" ማለት ነው።

በአላህ ሥሞች ማመን ከተውሒድ አንዱ ክፍል ነው። በአላህ ሥሞች እናምናለን፤ ማመን ብቻ ሊይደለም በትርጉማቸውም እንተማመናለን። ‹አል-ዐፉው› ይቅር ባይ ነው ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ይህንን ሥም ለራሱ የሠጠው ያለምክንያት አይደለም። በሥሙ ወደርሱ እንድንቃረብ ነው። በሥሙ ተስፋ እንድናደርግ ነው። የቱን ያህል ወንጀላችን ቢበዛም፣ የቱን ያህል ብናጠፋም፣ የቱን ያህል ብንከፋም አላህ ይቅር ይለናል፤ ያልፈናል፤ ይምረናል።

አላህ ይህን ሥም ለራሱ የሠጠው በምክንያት ነው። “ይቅርባይ” መሆኑን፤ ይቅር ባይነቱም እጅግ የሰፋ መሆኑን ለኛ ለባሮቹ ለማሳየት ነው። ይህም ተስፋ ቆርጠን ከሱ እንዳንርቅ ነው። አጥፍተናል አይምረንም ብለን ተሸማቀን ከጉያው እንዳንሸሽ ነው። ሥሞቹን ስናስታውስ ወደሱ ላለመቅረብ የምናቀርባቸው ምክንያቶች ሁሉ ይጠፋሉ፣ ሰበቦቻችን ቦታ ያጡና ድክመቶቻችን ብቻ ይቀራሉ። “አል-ዐፉው” የሚለውን ሥሙን ስናስታውስ በደማቅ ተስፋ እናንሠራራለን። ተሳስተን ጥፋት ላይ በወደቅን ቁጥር ይቅር ባይነቱን እናስባለን። ይህን ባናስብማ ኖሮ ተስፋ እንቆርጣለን፤ እንሸበራለን፤ በሐዘን እናልቃለን፣ በጭንቀት እንሞታለን።

ስናጠፋ ከሁሉ እና ከምንም ቀድመን አላህን ብቻ እናስብ። ሰዎች ስለኛ ጥፋት አብዝተው ቢናገሩም፤ ስለ ወንጀሎቻችን በሄዱበት ቢዘረዝሩም፣ ‘አላህ ኢይምረውም ኢይምራትም...’ ቢሉም አላህን ብቻ እናስብ። ጉዳያችንን እሱ ብቻ እንዲመለከት እንተው። በኛ እና በአላህ መካከል ሰዎች ምንም አያገባቸውም። ሰዎች እንደኛው የአላህ ባሮች እና ፍጡራን ናቸው። ብዙ ጥፋት እና ወንጀል አለባቸው። የኛም ሆነ የሌሎች ጉዳይ የሚወሰነው በፈጣሪያችን ነው። የሚቀጣንም ሆነ የሚምረን እሱ ነው። ስለሆነም ትልቁ እይታችን፣ ትኩረታችን እና ሀሳባችን ወደርሱ ሊሆን ይገባል።

አዎ ሌሎች ስለኛ ጥፋት እና ከፋት ብዙ ሊሉ ሊያወሩ ይችላሉ። ምንም ቢሉም አላህ ይቅር ይለናል። በአላህ እንተማመን፤ ከልብም እንመን፤ ይምረኝ ይሆን? ብለን አንጠራጠር። ይቅር እንደሚለንም እንተማመን። ከኛ የሚጠበቀው አውቆ ላለማጥፋት መሞከር፣ ካጠፉም ስህተትን ማመንና መፀፀት፣ ተስፋ ሳይቆርጡ ሁሌም ምህረቱን

መለመን፣ በወደቁ ቁጥር መነሳት ነው። ስናጠፋ ወደ አላህ ለመመለስ አንፍራ፣ እንሸማቀቅ። ስንፈጠር አጥፊዎች ሆነን ነው። በጥፋታችንና ወደ አላህ በመመለሳችን የአላህን መኖር እናምናለን፣ ጌትነቱን እንመሰክራለን። ባናጠፋማ ኖሮ አላህ እኛን እጥፍ፣ ሌሎች አጥፍተው ከሱ ምህረትን በሚለምኑ ሰዎች በተካን ነበር። ከዚህ እንፃር ኒያችንን እናስተካከል። አላህ ሊያኖረን እንጂ ሊያጠፋን አይደለም የፈጠረን። አላህ እኛን በመቅጣት የሚያተርፈው ነገር የለም።

እንፍራ፣ አንፈር። ሁሌም በአላህ ላይ ተስፋ እናድርግ። "ላ ኢላህ ኢልለላህ" ብሎ በአላህ ጌትነትና ብቸኛ ተመላኪነት የመሰከረ ሁሉ አላህ ዘንድ ብሥራት አለው። "ላ ኢላህ ኢልለላህ" ያለ ሁሉ ወዳጁ ነው። አላህ "ላ ኢላህ ኢልለላህ" ያለውን፣ ለሱ ያነነበለውን፣ የሰገደውን፣ የፆመውን፣ የሱን ውዴታ አስቦ የመፀወተውን፣ በተቻለ መጠን ሁሉ እርሱ .ያዘዘውን የፈፀመውን፣ ከከለከለው የተከለከለውን፣ እሱን ለመፍራት የቻለውን ያህል የታገለውን ባርያውንና ወዳጁን ወደ እሣት አይወረውርም። በፍፁም አይወረውርም።

ትንሽ ትልቅ ሳይባል ሁላችንም እናጠፋለን፣ ኃጢኣት በመሥራት ራሳችንን እንበድላለን፣ አላህ ያስቀመጠውን ድንበሩን በተደጋጋሚ እንጥሳለን፣ እንደ ህፃን ልጅ እንወድቃለን እንነሳለን። ግና ሁላችንም የምናውቀው አንድ ነገር አለ - ወላሂ ሁላችንም አምላካችንን እንወደዋለን፤ በኃጢኣት ተሸንፈን የፈፀምነውን ፈፀምን እንጂ ውስጣችን ይፈራዋል፣ ቢሆንልን ኖሮ ፍፁም በሆነ መልኩ አሱን መታዘዝ እንፈልጋለን።

እኛ ለአላህ ባሮቹ ነን። አላህን እንወደዋለን። እሱም ይወደናል፤ ስለሚወደንም እኮ ነው ብዙ ጥፋቶቻችን የሚሸፍንልን፤ በርካታ ነውሮቻችንን የሚደብቅልን። እያለፈንና ይቅር እያለን ነው እንጂ በየጥፋታችን ሁሉ ቢይዘንማ ኖሮ አንዳችንም ምድር ላይ ባልቀረን ነበር።

የምትወዱትን ሰው ስትወዱ ምን ያህል እንደምትወዱ ግለፁ ብትባሉ እንዴት ትገልፃላችሁ?...

አቡበከር አስ-ሲዲቅ (ረ.ዐ.) እና ነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እጅግ የሚዋደዱ የልብ ወዳጆች ናቸው። ታላቁ አቡበከር ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ነፍሳቸው እስክትወጣ ድረስ እጅግ አድርገው ይወዳሉ። በአንድ ሐሩር በበረታበት ቀን ጥም በረታባቸውና ከአንድ ቤት

ነራ ብለው ውሃ ጠጡ። አቡበከር ሁኔታውን ሲናገሩ "ነቢዩ ግጥም አድርገው ጠጡ፣ እኔ ረካሁ።" ይላሉ።

ነቢዩ እኔ ከራሳችሁ በላይ አስካልወደዳችሁ ድረስ አላመናችሁም ላሉት ንግግራቸው ጥሩ መግለጫ መሠለኝ። ከነፍሳችን በላይ፣ እጅግ የጠማው ሰው ውሃን ከሚወደው በላይ አላህን እንወዳለን። እኛ እንደምንወደው እንደምናውቀው ሁሉ አላህም እንደምንወደው ያውቃል።

"ኢይዞህ አትዘን አላህ አለ፣ አላህ ከኛ ጋር ነው።" ብሎ ያፅናናህ ሰው በርግጥም ወዳጄ ወዳጁን ማፅናናት ባለበት ትልቅ ነገር አፅናናህ።

ቃሉ የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እና አቡበከር ከአሳዳጅ ጠላቶቻቸው ከቁረይሾች ዋሻ ውስጥ በተደበቁበት ወቅት የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የተናገሩት ነው። "ላ ተሕዘን ኢንነላህ መዐና/አትዘን አላህ ከኛ ጋር ነው።"

ኢይዟችሁ አላህ ከኛ ጋር ነው። ኢይዟችሁ ለጊዜው ነው። የዱንያን ፈተናዎች አልፈን፣ አላህ ኃጢአቶቻችን ሁሉ ምሮን፣ ውዴታውን አጎናፅፎን፣ ጀነት ገብተን ከምንወዳቸው መልዕከተኞችንና ከደጋግ የአላህ ባሮች ጋር እንገናኛለን።

እጅግ አርግጠኛ ከምሆንባቸው ነገሮች መካከል አላህ (ሱ.ወ.) እኛን ባሮቹን ይወደናል፤ ስለሚወደንም እኮ ነው በሚደርስበን ትልቅ ሆነ ትንሽ መከራ ይመነዳናል፣ እየፈተነን ከወንጀላችን ያጥበናል፤ በመጨረሻም ነፃ ያደርገናል -አብሸሩ። ድሮ ወደነበርንበት የእናት አባታችን መቀመጫ ወደሆነው ጀነትም ይመልሰናል አብሸሩ።

የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) መጠጥ ደጋግሞ በመጠጣቱ ምክንያት ሰዎች የሰደቡትንና የረገሙትን ሰውዬ "አትርገሙት እሱ አላህን እና መልዕከተኛውን ይወዳል።" ብለዋል። እንዲሁም -"አላህ ይጠላዋል አትበሉ ፈተነው በሉ፤ አላህ ሆይ! ማረው አዘንለትም በሉ።" ብለዋል።

እኛም አላህ ምስከራችን ነው አላህን እንወደዋለን። አላህ ይቅር ይበለን፣ ምህረቱንም ይለግሰን።

ስለዚያ ምንም መልካም ነገር ሳይሠራ ጀነት ስለገባው ሰው እናስብ። ጥፋቱ እጅግ የበዛና ከልከ ያለፈ ነበርና አላህን ብርቱ ቅጣት እንዳይቀጣው ፈራና አቃጥሉኝና አላህ እንዳያገኘኝ ባህር ላይ በትኑኝ አለ። አቃጥለው ወደ አመድነት ሲለወጥ ውሃ ላይ

በተኑት። ሁሉን ቻዩ አላህ አመዱን ሰብስቦ ሰውዬውን እንደገና ሕያው አደረገው። "ለምንድነው ይህን ያደረግከው?" አለው። "ላንተ ያለኝ ፍራቻ ነው።" አለ። በዚሁ ፍራቻው ምክንያት አላህም ምህረቱን ለገሰው።

አላህ (ሱ.ወ.) የቻላችሁትን ያህል ፍሩኝ፣ የቻላችሁትን ያህል ከከለከልኳችሁ ተከልከሉ ነው ያለን። የቻልነውን ያህል እንፍራው። እንስገድ፣ እንውም፣ ከመጥፎ ነገሮች ሁሉ እንጠንቀቅ። አላህ (ሱ.ወ.) እናት ለልጇቿ ከምታገዝነው በላይ ያገዝንልናል።

እናም ከማንም በላይ የፈጠረንን አምላካችን እንመን። ከምንም በላይ የሱን እዝነት እንተማመን። እንፍራ፣ እናስብ፣ እንጨነቅ።

ማስታወሻ

ይህች ዓለም ባለቤት አላት። በዘፈቀደ አልተገኘችም። ድንገት አልተከሰተችም። ያቆማትና ያዋቀራት አምላክ አላት። ጌታዋ አላህ (ሱ.ወ.) ነው። እሱም ያስገኛቸውን ነገሮች ዝምብሎ አልበተናቸውም። ሁሉን ያያል፣ ይቆጣጠራል።

ምድር አምላኳ ፍትሃዊ አምላክ ነው። በደልን አይወድም። ሰዎች እንዲበዳደሉም አይፈቅድም። የበደሉና ግፍ የሠሩ ሰዎች ለጊዜው ያመለጡ ይመስላቸዋል እንጂ በደላቸው ተመዝግቧል፣ ሥራቸው ሁሉ ነገር ከሱ ድብቅ ባልሆነው ጌታ ዘንድ ሰፍሯል። የበደሉትና ግፍ የሠሩት፣ ያታለሉትና ያጭበረበሩት ጀዛቸው ቀኑን ጠብቆ ይከፈላል። በፍጥነትም ይሁን ዘግይቶ ሁሉም እንደየሥራቸው ይከሳሉ።

"ሁሉም ሰው ሌላውን ባጠጣው ነገር ያጠጣል" -ይላሉ። ሰው ይፍጠንም ይዘግይ የሥራውን ያገኛል፤ የእጁንም ይወስዳል፤ ይህም አላህ ስለመኖሩና ስለፍትሃዊነቱ ማሳያ። በግፍ የገደለ በግፍ ይሞታል።የሳቀ፣ የናቀ፣ ያላገጠ... ይሳቅበታል፣ ይናቃል፣ ይላገጥበታል።

- ✓ በግፍ ከዕድሜህ የተወሰነ ተሰርቆብህ ወደ እስር ቤት ተወርውረህ ሊሆን ይችላል፤ የሆነ ጊዜ ያሰረህ አካል መታሰሩ እንደማይቀር እርግጠኛ ሁን። የተዘጋብህ በር ይዘጋበታል።
- ✓ ሕይወትህን ሆነ ብሎ ያበላሸውን አካል አላህ ሕይወቱን ሳያበላሽበት እንደማይተወው እመን።